# ጠቃሚ መመሪያዎች

- በዚህ ችሎት ላይ ለመሳተፍ ከፈለጉ በችሎቱ ቀን እርስዎን ማግኘት የሚቻልበትን የስልክ ቁጥር ማስመዝገብ አለብዎት። ይህን ቀደም ሲል ቁጥርዎን ሰጥተውን ቢሆንም እንኳን ያድርጉ። በአስቸኳይ ሆኖም ችሎቱ ከሚሰማበት ቀን በፊት ያለው የስራ ቀን ከሰአት በኋላ ሳያልፍ ይመዝገቡ።

**<u>በኦንላይን ለመመዝገብ</u>**: ወደ **[https://va3.c2tinc.com/register/](https://va3.c2tinc.com/register/)** ይግቡ
በስልክ ከሚካሄድ ችሎት ማስታወቂያው የቀኝ የላይኛው ጎን ላይ "እንደ ጉዳይ ቁጥር" የተቀመጠውን "የመዝገብ ቁጥር" ያስገቡ። **ቁጥሮችን ብቻ እንጂ ፊደሎች ወይም ምልክቶችን አያስገቡ።** የምዝገባ መረጃ ያስገቡ። <u>የማረጋገጫ ቁጥርዎን ይጻፉ</u>።

**<u>በስልክ ለመመዝገብ</u>**: ቁጥርዎን ለማስመዝገብ በስልክ ቁጥር **(804) 786-3020** ወይም በነጻ የስልክ ጥሪ መስመር 1 (800) 552-4500 ይደውሉ። በሚመዘገቡበት ወቅት <u>የማረጋገጫ ቁጥርዎን ይጠይቁ።</u> ለመደወልዎ በማስረጃነት እንዲያገለግልዎ ይህን ቁጥር ሴቭ ያድርጉ።

- ችሎቱ በሚሰማበት ወቅት የስልክ መስመርዎን ነጻ ማድረግ እና ስልክዎ በቂ ባትሪ፣ ደቂቃዎች ያሉት መሆኑን እና በአካባቢዎ በቂ የአገልግሎት ሽፋን ያለ መሆኑን ማረጋገጥ የእርስዎ ኃላፊነት ነው።

- በሚደወልልዎ ወቅት አለመገኘትን ወይም በስልክዎ ላይ "የማይታወቁ ደዋዮችን" መዝጋትዎን አለመክፈትን ጨምሮ በማንኛውም ምክንያት ሲደወልልዎት የማያነሱ/ የማይመልሱ ከሆነ የመሳተፍ እድልዎ ያመልጥዎታል።

- በአካል መሳተፍ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ ጥያቄዎን ከችሎቱ ቀን በፊት ያስገቡ።

- በአባሪነት የተያያዙት በችሎትዎ ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሰነዶች ናቸው። ማስገባት የሚፈልጓቸው ተጨማሪ ሰነዶች ካሉዎት እነዚህን ለመጀመሪያ ደረጃ ይግባኝ ሰሚ <u>እና</u> ለተቃራኒው ወገን መላክ አለብዎት። ሰነዶቹ ለሁሉም ወገኖች ከችሎቱ *ቢያንስ ከሁለት ቀናት በፊት መድረስ አለባቸው።*

- **እነዚህን መመሪያዎች የማይከተሉ ከሆነ የማይደወልልዎ ከመሆኑም በተጨማሪ ችሎቱ እርስዎ ባልተገኙበት ይካሄዳል።**

ዕትም፡ ሕዳር 2017 ዓ.ም